ዳኞች፡ እትመት አሰፋ
ፀሐይ መንክር
ኑረዲን ከድር
መላኩ ካሳዬ
እስቲበል እንዱዓለም

አመልካች፡ አቶ መላይ ደርብ አረዶ

ተጠራ፡ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

መዝገቡ ተመርምሮ ብይኑ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀልን የሚመለከት ነው። ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበውም ተፈፀመ ከተባለው ድርጊት አኳያ አመልካች በወንጀል ህግ አንቀፅ 543(3) ስር ጥፋተኛ ተብሎ የመቀጣቱን አግባብነት መርምሮ ለመወሰን ነው።

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ የካቲት 24/2014 ዓ.ም ፅፎ በአሁን አመልካች ላይ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፌንፌኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ሱልልታ ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ ነው። የክሱም ዝርዝር አመልካች የወንጀል ህግ አንቅፅ 543(3) እና የትራፊክ ደንብን ለመቆጣጠር በክልሉ መንግስት የወጣውን ደንብ ቁጥር 194/2009 አንቀጽ 8(1) እና 27(1) ድንጋጌን በመተላለፍ በክሱ ዝርዝር በተገለፀው ቀን፣ ቦታ እና ሰዓት ግልፅ የትራፊክ ደንብን በመተላለፍ መንገድ በማቋረጥ ላይ ለነበረችው ሟች ቅድስት ዳኜ ለተባለችው እግረኛ ቅድሚያ በመከልከል ሲያሽከረክር በነበረው የሰሌዳ ቁጥር 3-A04086 ET ሲኖትራክ የሞኖት ተሽከርካሪ በተሽከርካሪው የፊት አካል የግራ ጎን ገጭቶ የገደለ በመሆኑ የሙያ ኃላፊነቱን በማጓደል በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል ተከስሷል የሚል ነው።

የአሁን አመልካች ለዚሁ ክስ በሰጠው መልስ ከፊት ለፊቱ ቆሞ ከነበረው ቀያ ዶልፊን ተሽከርካሪ ስር በርካታ ልጆች ከግራ ወደ ቀኝ መንገድ ለማቋረጥ ግር ብለው ወደ አስፋልቱ ሲገቡበት እነርሱን ለማዳን መሪ ሲጠቀም መንገዱን በማቋረጥ ላይ የነበረችው ሟች ወደኋላ ተመልሳ የገባችበት መሆኑን ገልፆ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ከጥፋተኝነት እንዲር መብቱን ጠብቆ የተከራከረ መሆኑን የሰር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል።

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የዐቃቤ ህግን ክርክር እና ማስረጃን ከሰማ በኋላ አመልካች በተከሰሰበት አንቀፅ ስር እንዲከላከል ብይን ሰጥቷል። በኋላም የአመልካቹን መከላከያ ሰምቶ "አልተከላከለም" በሚል በዚሁ አንቀፅ ስር ጥፋተኛ ብሎት በ3(ሶስት) ዓመት ከ7(ሰባት) ወር እስራት እና በብር 2,000(ሁለት ሺህ ብር) የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጣ ወሰንቧል። ይኸው ውሳኔ እስከ ከልሱ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ፀንቷል።

የእሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ነው። አመልካች ሐምሌ 04/2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈጽሟል ያለውን መሰረታዊ የሆነ ስህተት ጠቅሶ በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል። የቀረበው ሰበር አቤቱታ ተመርምር ከላይ በዚህ ፍርድ መዝጊያ ላይ የተጠቀሰውን ነጥብ ግራ ቀኙ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ታዝዞ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል።

ከክርክሩ አመጣጥ መረዳት እንደተቻለው የወንጀል ህግ አንቀፅ 543(3) ተጠቅሶ አመልካች ላይ ክስ የቀረበው ግልፅ የሆነ የትራፊክ ደንብን በመተላለፍ ለእግረኛ ቅድሚያ በመከልከል መንገድ በማቋረጥ ላይ የነበረችን እግረኛ ጉዮቶ ገድሏል በሚል ነው። ተጥሏል የተባለው ግልፅ የትራፊክ ደንብ ደግሞ የከለሉ የትራፊክ ደንብ ቁጥር 194/2009 አንቀፅ 8(1) እና 27(1) ነው። የዚህ ደንብ አንቀፅ 8(1) የሚደነግገው ስለእሽከርካሪዎች የመንገድ አጠቃቀም ሲሆን አንቀጽ 27(1) ደግሞ ለእግረኛ ቅድሚያ መስጠት የሚገባ መሆኑን ነው። በዚሁ መሰረት ማንኛውም አሽከርካሪ የትራፊክ መንገድ ሲጠቀም በሰው እና በንብረት ላይ ጉዳይ በማያደርስ አኳኋን በጥንቃቄ ማሽከርከር ያለበት ስለመሆኑ እና መንገድ ለሚያቋርጥ እግረኛም ቅድሚያ መስጠት የሚገባው ስለመሆኑ ሁለቱ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ።

ሆኖም የእግረኛ ማቋረጫ በሌለበት ስፍራ የተሽከርካሪ መንገድ ለሚያቋርጥ እግረኛ ቅድሚያ መከልከል በወንጀል የሚያስጠይቀው በወንጀል ህግ አንቀፅ 543(2) ወይስ በንዑስ አንቀፅ (3) ስር ነው የሚለው መታየት ያለበት ጉዳይ ነው። በመሰረቱ መንገድ ለሚያቋርጥ እግረኛ ቅድሚያ መከልከል የአሽከርካሪውን የጥንቃቄ ጉድለት የሚያሳይ በመሆኑ በሁለቱም ንዑሳን አንቀፆች ስር ጥፋት ቢሆን የቸልተኝነት ወንጀል የሚያስቀጣ ነው። በድንጋጌው ንዑስ አንቀፅ (3) ስር ያለው የወንጀል ተጠያቂነት የሚመነጨው አሽከርካሪው ድርጊቱን የፈጸመው ግልፅ የሆነ የትራፊክ ደንብን በመተላለፍ ስለመሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ የዚሁ ድንጋጌ ይዘት ያስገነዝባል። እዚህ ላይ ለእግረኛ ቅድሚያ ከመከልከል ጋር ተያይዞ "ግልፅ የሆነ የትራፊክ ደንብን በመተላለፍ" የሚለው ሀረግ የሚገለፀው ጉዳት በደረሰበት ስፍራ ለመንገድ ተጠቃሚዎች ሊደረግ ስለሚገባ ጥንቃቄ የሚገልፅ እንደ እግረኛ ማቋረጫ ያሉ ልዩ የትራፊክ ምልክት መመሪያዎችን ባለመከተል የተፈፀሙ የጥንቃቄ ጉድለቶችን ነው። ጉዳት በደረሰበት ስፍራ በዚህ መልኩ የተቀመጠ ግልፅ የመንገድ ላይ

የትራፊክ ምልክት አልያም ከጥቃቱ አኳያ ሊወሰድ ስለሚገባ ልዩ የትራፊክ መመሪያ በሌለበት ለእግረኛ ቅድሚያ በመከልከል ጉዳት ማድረስ በወንጀል ሀጉ አንቀፅ 543(2) ስር ከሚያስጠይቅ በተር "ግልፅ የትራፊክ ደንብን በመተላለፍ የተፈፀመ ነው" የሚያሰብል አይደለም።

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካች የተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት በተፈፀመበት ስፍራ የእግረኛ ማቋረጫ መንገድ ስለመኖሩ የቀረበው ክስ የሚገልፀው ነገር የለም። አመልካችም ቢሆን የወንጀል ህግ አንቀፅ 543(3) ተጠቅሶ ክስ የቀረበበት በእግረኛ ማቋረጫ ስፍራ ለመንገደኛ ቅድሚያ በመከልከል የሞት ጉዳት አድርሷል በሚል ሳይሆን በደፈናው መንገድ ለሚያቋርጥ መንገደኛ ቅድሚያ ከልክሏል በሚል ነው። የእግረኛ ማቋረጫ መንገድ በሌለበት ስፍራ መንገድ ለሚያቋርጥ እግረኛ ቅድሚያ በመከልከል የሚደርስ የሞት ጉዳት ደግሞ በወንጀል ህግ አንቀፅ 543(2) ስር እንጂ በንዑስ አንቀፅ (3) ስር የማያስጠይቅ ስለመሆኑ ከላይ አቋም የተያዘበት ጉዳይ ነው። ከዚህ አንፃር አመልካች ፈፀመ ለተባለው የቸልተኝነት ወንጀል በወንጀል ህግ አንቀፅ 543(2) ስር ጥፋተኛ መባል ሲገባው የሰር ዳኮድ ቤቶች በድንገጊው ንዑስ አንቀፅ (3) ስር ጥፋተኛ ማለታቸው በሁለቱ ንዑሳን አንቀፆች መካከል ያለውን መሰረታዊ የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገርን መሰረት ያላደረገ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት ሆኖ ተገኝቷል።

በመሆኑም የሰር ዳኮድ ቤቶች በወንጀል ህግ አንቀፅ 543(3) ስር በአመልካች ላይ ያስተላለፉት የጥፋተኝነት ውሳኔ በወንጀል ህግ አንቀፅ 195(2(ለ(2))) መሰረት ተሻሽሎ አመልካች ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ህግ አንቀፅ 543(2) ስር ነው ተብሏል።

ከትላት አንፃር አመልካች ጥፋተኛ ለተባለበት አንቀፅ ስራ ላይ ባለው የትላት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 ደረጃ እና እርከን የወጣለት ነው። በወንጀል ህጉ አንቀፅ 543(2) ስር ትላት ከመወሰኑ በፊት የቸልተኝነት ደረጃው ሊለይ እንደሚገባ መመሪያው ያሳል። ይህንኑ ለመለየት አመልካች የተከሳሽነት ቃሉን ሲሰጥ የገለፃቸው አነባቢያዊ ሁኔታዎች በመነሻነት ተይዘዋል። በዚሁ አግባብ ድርጊቱ በተፈፀመበት ስፍራ ሌላ ተሽከርካሪ የነበረ ስለመሆኑ እና በአነባቢው ተርካታ ሀሳናት ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ለመሆኑ አመልካች በራሱ ገልፀዋል። አንድ አሽከርካሪ በእንደዚህ ዓይነት ስፍራ ሲያሽከረክር ከሌላው ጊዜ እና ስፍራ በተለየ አኳኋን ጥንቃቄ ማድረግ የሚገባው በመሆኑ አመልካች ጉዳቱን ያደረሰው ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ አይደርስም በሚል ግምት ወይም ባለማመዛዘን እንደሆነ ግንዛቤ የሚያስወስድ ነው። ስለሆነም የአመልካች የቸልተኝነት ደረጃ "ተራ ቸልተኝነት" በሚለው ተወስዷል። ሟች የእግረኛ ማቋረጫ መንገድ በሌለበት ስፍራ መንገድ ለማቋረጥ ከመሞከሯም ውጭ በድርጊቱ አፈፃፀም ውስጥ የሟች አስተዋጽኦ የነበረ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ነገር ባለመኖሩ ለጉዳቱ መድረስ የሟች አስተዋፅዖ የለም በሚለው ተወስዷል።

በመሆኑም በመመሪያው ክፍል 3 ንዑስ ክፍል 1 እና አባሪ 1 መሰረት የወንጀል ደረጃው 4፣ የእስራት መነሻ እርከን 16 እና መቀጮ እርከን 4 መሆኑ ተለያይቷል። ለዚህ እርከን የተቀመጠው ቅጣትም ከ3 ዓመት እስከ 3 ዓመት ከ7 ወር እስራት እና እስከ ብር 5,000(አምስት ሺህ) የሚደርስ መቀጮ ነው። ስለሆነም የ3(ሶስት) ዓመት እስራት እና ብር 3,000(ሶስት ሺህ ብር) የገንዘብ ቅጣት

በመነሻ ቅጣትነት ተያዘ በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኙት የቅጣት አስተያየቶች ታይተዋል። በዚሁ መሰረት በአመልካች ላይ የቀረበ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የሌለ ሲሆን በጠቅላላው ሶስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ለአመልካች የተያዙ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት መዝገብ የሚያሳይ በመሆኑ ማቅለያ ምክንያቶቹ በዚህ ችሎትም ተወስደው የቅጣት እርከኑ ወደ አስራት እርከን 13 እና መቀሌ እርከን 1 ዝቅ ብሏል። በዚህ እርከን ስር ያለው ቅጣት ከ2 ዓመት ከ3 ወር እስከ 2 ዓመት ከ9 ወር እስራት እና እስከ ብር 1000 የሚደርስ መቀጮ ነው። ስለሆነም በተቀመጠው ፍቅደ ሰልጣን ውስጥ አመልካች በ2(ሁለት) ዓመት ከ3(ሶስት) ወር ፅኑ እስራት እና ብር 1,000(አንድ ሺህ ብር) የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጣ ተወስኗል።

ውሳኔ

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ሱሉልታ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/78303 ላይ የካቲት 30/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰጥቶ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ በመ/ቁ/404246፣ ላይ ሰኔ 09/2014 ዓ.ም የፀናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195(2(ለ(2))) መሰረት ተሻሽሏል።

2. ከተፈፀመው ድርጊት እና ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር አኳያ አመልካች ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው በወንጀል ህግ አንቀፅ 543(2) ድንጋጌ ስር ነው ተብሏል።

3. በውሳኔ ተራ ቁጥር 2 ስር በተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረት ቅጣቱ ተሰልቶ አመልካች በጠቅላላው በ2(ሁለት) ዓመት ከ3(ሶስት) ወር ፅኑ እስራት እና በብር 1,000(አንድ ሺህ ብር) የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጣ ተወስኗል።

ትዕዛዝ

1. የክልሉ ማረሚያ ቤት አስተዳደር በተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሰረት አመልካች በዚህ ጉዳይ እስከ ዛሬ የታሰረውን በቅጣቱ በማስላት ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ይፃፍ።

2. መዝገቡ ተዘግቷል። ይመለስ።


Click Ethiopian Laws